Maryland's Largest School District

**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**



Summer RISE
Connecting Students to Careers

# ሠመር ራይዝ Summer RISE 2024 የተማሪ ስምምነት Student Agreement

Department of Partnerships
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
850 Hungerford Drive, Room 159, Rockville, Maryland 20850

## PARENT/GUARDIAN/ELIGIBLE STUDENT CONSENT የወላጅ/ሞግዚት/ብቁ ተማሪ ስምምነት

የሠመር ራይዝ 2024 ፕሮግራም የተነደፈው በአሁኑ ወቅት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ለሚማሩ ወጣት ጁንየሮች እና ሲንየሮች በ 2024 ሠመር የሙያ ትምህርት እውቀት የሚገበዩበት ልምድ እድሎችን ለማመቻቸት ነው። ለሠመር ራይዝ ፕሮግራም የምመዘገበው 2024-2025 የትምህርት ዓመት MCPS 11ኛ ክፍል ጁንየር ተማሪ ወይም 12ኛ ክፍል ሲንየር ተማሪ ስለምሆን ብቁ መሆኔን እርግጠኛ ስለሆንኩ ነው። ከወላጆቼ/ከአሳዳጊዬ ጋር በአንድነት ተስማምተን በሠመር ራይዝ ፕሮግራም ለመሳተፍ ሙሉ ኃላፊነት እወስዳለሁ።

1. ጁን 24, 2024 ተጀምሮ ጁላይ 26, 2024 የሚያበቃው የሠመር ራይዝ መርሃ ግብር -በተመደብኩበት የንግድ ኩባንያ፣ ድርጅት፣ ኤጀንሲ፣ ተቋም፣ ("የሙያ ሥራ ልምድ የሚሰጥ ተቀባይ አስተናጋጅ ድርጅት") ጣቢያ፣ ወይም ቨርቹዋል ("የሙያ ልምድ") ላይ የተመሰረተ የመግር እድል።እስከ 5 ሳምንታት ድረስ የሚከናወን እና ቢያንስ ለ50 ሰአታት በተግባር የሚሠራ ስራ መሆኑን ተገንዝቤአለሁ። የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊ በመሆን በቀን ከ8 ሰአት ያልበለጠ እና በሳምንት ከ40 ሰአታት የማይበልጥ ጊዜ በሙያ ልምምድ ቦታ እንደማሳልፍ ተረድቻለሁ። የሥራ ልምምዱ ከሰኞ እስከ አርብ ከጠዋቱ 7፡00 A.M. እስከ 6፡00 P.M. ሊካሄድ ይችላል። ከነዚህ ሰአታት ውጭ ለመሳተፍ ከመረጥኩ፣ ከቀኑ 9፡00 P.M. በኋላ መስራት የማልችል በመሆኑ፣ ለእኔ የስራ ልምምድ እድል ለመስጠት የሚቀበለኝ ተቋም ለሠመር ራይዝ ማስተባበሪያ ቢሮ በቅድሚያ ሊገለጽለት ይገባል። የእኔ መርሃ ግብር ከመጀመሩ አስቀድሞ በአስተናጋጁ ተቋም የሚወሰን ሲሆን ለእኔ ማረጋገጫ ይገለጽልኛል። የሚጠበቀውን የተማሪ አበል ለማግኘት በሙያ ክህሎት እና በፋይናንስ ትምህርት አውደ ጥናት ላይ 50 ሰአት መሳተፍ እና ማጠናቀቅ ይጠበቅብኛል። ከሙያ ልምድ ሰጪው አካል የሚመለከተ(ታቸ) ው የሥራ ባልደረባ(ዎች) (“Career Experience Host Designee(s)”) የሠመር ራይዝ ፕሮግራሙ ሲጠናቀቅ ተቀባይነት ያለው 50-ሠዓት የሙያ ሥራ ልምምድ ማረጋገጫ ይሰጣል።
2. ለሠመር ራይዝ ፕሮግራም ከመመዝገቤ በፊት ሶስት ዋና ዋና ምርጫዎቼን በመለየት ረገድ የሙያ ስራ ልምምድ ምደባዬን በሚመለከት የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ቡድንን ለመርዳት "CAREER INTEREST PROFILER እና CAREER CLUSTER FINDER በ NAVIANCE" መተግበሪያ ላይ መውሰድ እንዳለብኝ ተረድቻለሁ
3. ሠመር ራይዝ ከመጀመሬ በፊት በሠመር ራይዝ ፕሮግራም ላይ ለመሳተፍ የወላጅ/አሳዳጊ ስምምነትን ማረጋገጥ እና በቀጥታ በአካል ወይም ቨርቹወል ሙያዊ ክህሎቶችን እና የፋይናንስ እውቀት አውደ ጥናት ላይ መሳተፍ እንዳለብኝ ተረድቻለሁ። አውደ ጥናቱ የሚካሄደው ከሚፈለገው የፕሮግራም ሰአታት በተጨማሪ ነው። የስልጠናው ዝርዝር በኢ-ሜይል እንደሚላክልኝ ተገልጾልኛል።
4. እኔ በአካል የሙያ ልምምድ ማድረግ ካለብኝ፥ የሙያ ልምምድ እስከምወስድበት ቦታ ድረስ የመጓጓዣ ኃላፊነቱ የራሴ መሆኑን ተገንዝቤአለሁ። (5–18 እድሜ) ያላቸው ተማሪዎች በሙሉ በሞንትጎመሪ ካውንቲ "Youth Cruiser SmarTrip card" በመያዝ "Ride On"፣ "Ride On Flex" እና አንዳንድ ሜትሮባስ "Metrobus" መስመሮችን በነፃ ለመጠቀም ይችላሉ። የስማርት ትሪፕ ካርዶች "SmarTrip cards" ማመልከቻ በትምህርት ቤቱ እና በሌሎች ቦታዎችም ይገኛል። "Youth Cruiser SmarTrip" ካርድ ስለማግኘት የበለጠ መረጃ ለማግኘት የኮሌጅ/የሙያ ስራ መረጃ አስተባባሪዎን ያነጋግሩ እና/ወይም የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትራንስፖርት መምሪያ ድረ ገጽ www.montgomerycountymd.gov/DOT-Transit/kidsridefree/ ይጎብኙ።
5. የሙያ ልምምድ ምደባ የሚደረገው በእኔ የሙያ ፍላጎት፣ በመልክዓ ምድራዊ የመኖርያ አካባቢ፣ በአካል፤ እና/ወይም ቨርቹወል ምርጫዬን መሠረት በማድረግ ሲሆን እንደመገኘቱ ሁኔታ የሚወሰን መሆኑን ተገንዝቤአለሁ።
6. የሠመር ራይዝ ፕሮግራምን በሚመለከት ወቅታዊ መግለጫ ኢሜይል እንደሚደረግልኝ እና "non-MCPS እና የ MCPS ኢሜይል" አድራሻዎቼን ከሠመር ራይዝ ጽ/ቤት ከተነገረኝ በኋላ በየቀኑ ማየት-መከታተል እንዳለብኝ ገብቶኛል።
7. የእኔን መርኃግብር በሚመለከት ከሙያ ልምምድ ሰጪ የሚመለከተው ሠራተኛ ወይም ተወካይ (my "Career Experience Host Designee(s)") ጋር በቀጥታ የማስተባበር ኃላፊነት እንዳለብኝ ተገንዝቤአለሁ።
8. በጥሩ ሁኔታ ለመከታተል፥ ጥሩ ስነምግባር፥ ትክክለኛነት፥ ሥነ ሥርዓት፥ በፍጥነት መሥራት፥ አስተዋይነት፥ ተገቢ አለባበስ፥ እና አግባብነት ባለው የቢዝነስ ስነ-ምግባር እና ቨርቹወል የምሳተፍ ከሆነ፣ ቪድኦ ላይ መሆን እንደሚጠበቅብኝ ተስማምቻለሁ። በእኔ የስራ ልምምድ አስተናጋጅ ተወካይ(ዎች) ሊፈቱ የማይችሉ ጉዳዮች ካጋጠሙኝ ወይም ስጋቶች ካሉኝ፣የእኔን የሠመር ራይዝ አስተማሪ አገናኝ ወይም MCPS Summer RISE Program office summer-rise@ mcpsmd.org ወይም 240-740-5599 በመደወል ማግኘት እችላለሁ።
9. በአካል በተገኘ የስራ ልምምድ ለመሳተፍ ከመረጥኩ፣ የእኔ የሠመር ራይዝ አስተማሪ ተባባሪ/ረዳት ወይም የሠመር ራይዝ ሰራተኞች የእኔን የሥራ ልምምድ በርቀት የመቆጣጠር አማራጭ እንደሚኖራቸው ተረድቻለሁ።
10. እኔን የስራ ልምምድ እንዳደርግ የሚቀበለኝ ተቋም ማጣሪያ እና ክትባቶችን ጨምሮ ሌሎች ተጨማሪ መስፈርቶች ሊኖሩት እንደሚችል ተረድቻለሁ። ከጁን 24 የሠመር ራይዝ ፕሮግራም መጀመሪያ ቀን በፊት ማንኛውንም ተጨማሪ የማጣሪያ መስፈርቶችን ለማሟላት ከእኔ የስራ ልምምድ አስተናጋጅ ተወካይ(ዎች) ጋር መስራት የኔ ሃላፊነት ነው። የአስተናጋጁን መስፈርቶች ማሟላት ካልቻልኩ፣ ከተገኘ ሌላ እድል እስከሚሰጠኝ እጠብቃለሁ።
11. በሰመር ራይዝ ፕሮግራም ላይ በአካል ለመሳተፍ ከመረጥኩ ከኮቪድ-19 ጋር የተያያዙ ማናቸውም ገደቦች እንዳሉ ሆነው የምሳተፈው በወላጅ/አሳዳጊ ፈቅድ ተሰጥቶኝ በፈቃደኝነት እንደምሠራ ተረድቻለሁ፣ ተስማምቻለሁ። በተቻለ መጠን፣ የሙያ ሥራ ልምምድ ተቀባይ አስተናጋጆች ተወካይ(ዎች) በሞንትጎመሪ ካውንቲ አስተዳደር እና በ MCPS የተቀመጡትን የኮቪድ-19 ፕሮቶኮሎች መከተል አለባቸው። ለኮቪድ-19 ለተጋለጠ(ች) ተማሪ MCPS ምንም አይነት ሃላፊነት እንደማይወስድ ተገንዝቤአለሁ።

12. በእኔ የስራ ልምምድ አስተናጋጅ ድርጅት ቅጥር ሰራተኛ እንደማልሆን ተረድቻለሁ። የሥራ ልምድ የሚሰጠኝ ድርጅት ከሠመር ራይዝ ተሳታፊዎች ወዲያውኑ የሚያገኘው ምንም አይነት ጥቅም አይኖርም፣ እናም አንዳንዴ ሥራቸው እንኳ ሊስተጓጎል ይችላል። በእኔ የስራ ልምምድ አስተናጋጅ ስራዎች ላይ በቀጥታ እንደማልሳተፍ ወይም በመደበኛነት ወይም በቀጣይነት ስራ እንደማልሰራ (ፋይል ማደራጀት፣ ሌላ የፅህፈት ስራ ወይም ደንበኞችን ማስተናገድ) በመሳሰሉት ስራዎች ላይ እንደማልሳተፍ ተረድቻለሁ። ለእኔ የሙያ ልምምድ የሚሰጠኝ ተወካይ የቢዝነስ/የድርጅቱን አጠቃላይ እንቅስቃሴዎች የሚመለከት መግለጫ ይሰጡኛል፥ የእኔን ሚና፥ ኃላፊነቶች፥ እና ለቢዝነሱ/ለድርጅቱ ማከናወን ያለብኝን ተግባሮች ያስተምሩኛል። ሥራ አስፈጻሚው(ዋ) ወይም ማኔጀር በሚሠራው ሥራ ዉጤታማ በሆነ መንገድ ለመከወን የሚጠቀምበትን ስልት፣ ጥራት፣ ክህሎት፣ እና እውቀትን በጥልቀት በመሻት እነዚህን ተግባራት እፈጽማለሁ። በበርካታ የሥራ ቅጥር አካባቢዎች መጠቀም የምችለዉን ሙያ ለመማር እድል ይኖረኛል።

13. ስለ እኔ የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሞክሮ ቅድመ ዳሰሳ እና የፕሮግራም መጨረሻ ዳሰሳ ለማቅረብ ተስማምቻለሁ።

14. የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎች ፕሮግራሙን በተሳካ ሁኔታ ሲያጠናቅቁ ባጀቱ ከተገኘ ለፕሮግራሙ ወጪዎች እንደ ማካካሻ ተደርጎ የሚሰጣቸውን አበል ማግኘት እንደሚችሉ በመገንዘብ ተስማምቻለሁ። የሠመር ራይዝ ፕሮግራምን እንደጨረስኩ MCPS ከወላጅ/ከአሳዳጊ ፍቃድ ከተሰጠ በኋላ የአበል ቼክ ለማዘጋጀት ለሚያስተዳድረው ባንክን የመጀመሪያ እና የመጨረሻ ስሜን ያስተላልፋል። የድጎማ ቼኩ ክፍያ የሚፈፀመው በቂ የገንዘብ ድጋፍ መገኘት ላይ የተመሰረተ እና ዝቅተኛው 50-ሰአት መስፈርት ተሟልቶ መጠናቀቁ በሠመር ራይዝ ፕሮግራም ጽ/ቤት ከተረጋገጠ በኋላ ፕሮግራሙ እስኪጠናቀቅ ድረስ እንደማይከፈል ተረድቻለሁ። ቼክ ለመውሰድ በጋራ የሚመች ጊዜ አስቀድሞ ቀጠሮ ማስያዝ ያስፈልጋል። summer-rise@mcpsmd.org የእኔን ሠመር ራይዝ አስተማሪ አገናኝ መኮንን ወይም "Summer RISE Program office" ማግኘት እችላለሁ፥ ወይም የተማሪ አበል ክፍያን በተመለከተ 240-740-5599 በመደወል ጥያቄ ማቅረብ እችላለሁ።

15. በሠመር ራይዝ ፕሮግራም ላይ መሳተፍ ከስራ ልምምድ አስተናጋጅ ጋር በመደበኛነት እንድሰራ መብት እንደማይሰጠኝ እና በተቀጣሪነት ለመቀጠር ምንም መጠበቅ እንደሌለብኝ ተረድቻለሁ።

16. በሠመር ራይዝ ፕሮግራም ወቅት ቪዲዮ ለመቀረጽ፣ ፎቶግራፍ ለመነሳት እና/ወይም ለመቀረጽ የወላጅ/የአሳዳጊ ፈቃድ እንደሚያስፈልገኝ ተረድቻለሁ። ምስሎቹ እና/ወይም ሪኮርዶቹ ስለ ሠመር ራይዝ ለማስተዋወቅ ያለተጨማሪ መግለጫ ለተለያዩ ዓላማዎች ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ተስማምቻለሁ። በእነዚህ አጠቃቀሞች ምክንያት ምንም ክፍያ እንደማይሰጠኝ እና ምስሎቹ፣ ቪድዎቹ፣ ሪኮርዶቹ፣ እንዲሁም ማናቸውም በዚህ ምክንያት የሚፈጠሩ ሥራዎች ባለቤትነቱ የ MCPS መሆኑን እገነዘባለሁ።

17. የእኔ የስራ ልምምድ አስተናጋጅ ተወካይ(ዎች) በሙያ ልምምድ ወቅት ስላለኝ ተሳትፎ ለ MCPS መረጃ ማጋራት እንደሚችሉ ተረድቻለሁ። የእኔ የስራ ልምምድ አስተናጋጅ ወይም ተወካይ የሠመር ራይዝ ተሳታፊዎችን የሚመለከት ምንም አይነት መረጃ ለሦስተኛ ወገን አያጋራም።

18. የዚህን ስምምነት ውል፣ በስራ ልምምድ ተቀባይ አስተናጋጅ የተሰጡ ህጎች እና መመሪያዎችን፣ወይም ማንኛውም ሌላ የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ደንቦች፣የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ህጎችን ለማክበር ካልቻልኩ ከሥራ ልምምድ ፕሮግራም ልወገድ እችላለሁ እና ድጎማውን ለመቀበልም ብቁ እንደማልሆን ተገንዝቤአለሁ።

19. የሚያሳስበኝ ነገር ካለ ስለ ሙያ ልምምድ፣ በፍጥነት ወደ "my Summer RISE" አስተማሪ ወይም ለ "Summer RISE Program office" በዚህ በይነመረብ ላይ summer-rise@mcpsmd.org ወይም 240-740-5599 በመደወል ሪፖርት ማድረግ አለብኝ።

ስለ "Summer RISE 2024 Student Agreement" ለማመልከት የተማሪ ስምምነት ቅጽ በመመዝገቢያ ፎርም ላይ ባለዉ ሳጥን ምልክት እንዲደረግ ይገለጻል፣ እናም ይህ በኤክትሮኒክስ የምታቀርበ(ቢ)ው ስምምነት እና የኤሌክትሮኒክስ ፊርማ ከግል ፊርማህ(ሽ) ጋር እኩል መሆኑን እንደተገነዘብክ(ሽ) ይቆጠራል።